የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
**Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy**
Tel +44 208 1335670 org @ginbot7.org

---

**ጥር 24 2001**

*ጋዜጣዊ መግለጫ*

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የመጀመሪያውን ጠቅላላ ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ፡፡**

ቅዳሜ ጥር 23 2001 ኢ.ም የግንቦት 7 ንቅናቄ የመጀመሪያውን ጠቅላላ ጉባኤ አደረገ፡፡

በእዚህ ጉባኤ ንቅናቄው ተሻሽሎ የቀረበውን ህገ-ደንብ በቋሚነት አጸደቀ፡፡ እስካሁን በጊዜያዊነት ሲያገለግሉ የነበሩትን የስራ አመራር አባላት፣ በሚቀጥለው ሁለት አመታት በቋሚነት በሚያገለግሉ በምርጫ በተሰየሙ የንቅናቄው ማእከላዊ የስራ አመራር አባላት ተካ፡፡

ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ ቸኮል ጌታሁንና አቶ ዳንኤል አሰፋ፣ የቀድሞው ጊዚያዊ ማእከላዊ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የነበሩ ሲሆን፣ አሁንም ለአዲሱ ኮሚቴ በአባልነት ተመርጠዋል፡፡ በሌላ መልኩ በአደባባይ በግንቦት 7 አባልነታቸው ከሚታወቁት መሃል አቶ ኤፍሬም ማዴቦና አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል፣ የማእከላዊ የስራ አመራር አባላት ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ከተቀሩት ሌሎች ተመራጮች መሃል አንዲት ሴት የስራ አመራሩ አባል ሆነዋል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው የንቅናቄውን ሁለገብ የትግል ስልትና የንቅናቄውን ይፋና ህቡእ የሆነ አደረጃጀት ግምት ውስጥ በማስገባት ማእከላዊ አመራሩ ስራን በጥንቃቄና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀበት መንገድ መፈጸም እንዲችል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመወሰንና የማስፈጸም ሙሉ ውክልና ለአዲሱ አመራር ሰጥቶታል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤው የግንቦት 7 ንቅናቄ የሚያደርገው ትግል በአባላትና በአመራሩ መሃከል በከፍተኛ መተመማን ላይ የተመሰረተ መሆኑን በማስታወስ አመራሩ የተሰጠውን ከፍተኛ ስልጣን በአግባቡ የሚጠቀም እንደሚሆን ያለውን እምነት ገልጽዋል፡፡ ይህ የውክልና ስልጣን ንቅናቄው በምስረታው ወቅት ባወጣው ሰነድ ላይ ተመስርቶ፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት ሀገረ-ኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግላቸው ቀጠና አድርገው ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር በጋራ የመስራት መርህ አጥብቆ በመያዝ፣ የመለሰን እብሪተኛ አገዛዝ ለማስወገድ አመራሩ ከተለያዩ ለዴሞክራሲ ከቆሙ ድርጅቶች ጋር ትብብሮችን በአስቸኳይ በመፍጥር እንዲንቀሳቀስ ሙሉ መብት ሰጥቶታል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው፣ የግንቦት 7 ንቅናቄ እስካሁን በሃገሪቱ ወስጥ የሚገኘውን የዘውግ፣ የእምነት፣ የጾታ፣ የእድሜና ሌሎቸም የማህበራዊና የኢኮኖሚ ፍላጎቶች ስብጥር ለማካተት ያደረገውን ጥረት በማድነቅ፣ ወደፊትም ይህ ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች ሁለንተናዊ ስብጥር ግምት ውስጥ ያስገባ፣ አባላትና ደጋፊዎች የማሰባሰቡን ስራ አዲሱ የስራ አመራር በትጋት እንዲሰራ የተለየ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው ንቅናቄው በአጭር ግዜ ውስጥ ያስመዘገበውን የስራ ውጤት በማድነቅ ነገር ግን ይህ የስራ ውጤት የሁላችንንም ነጻነት ለማስከበር ከሚጠብቀን ስራ ጋር ሲነጻጸር ሊያኩራራን የሚገባ እንዳልሆነ አስምሮበታል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው ግንቦት 7 በአጭር ግዜ ላስመዘገበው የስራ ውጤት የአባላቱን ታታሪነት ያደነቀ ሲሆን፣ በተለይ ግን በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ለንቅናቄው እጅግ ቀና የሆነ መንፈስ ከማሳየት አንስተው፣ በገንዘባቸው በእውቀታቸው በጉልበታቸው መስዋእትንት

በመክፍል ያበረከቱት አስተወጽኦ ንቅናቄው ላስመዘገበው እድገት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ እንደሆነ ግልጽ አድርጎታል፡፡

በመጨረሻም ጠቅላላ ጉባኤው፣ ንቅናቄው ከህዝብ የሚያገኘው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪውን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን በማቅረብ፣ ህዝብ በአመኔታ ለንቅናቄው የሚሰጠው ድጋፍ የመለስ ዜናዊን አምባገነናዊ አገዛዝ በአጭር ግዜ ውስጥ የመጨረሻው የሃገራችን አምባገነን አገዛዝ እንዲሆን በማድረግ፣ ይህን ብካይ አምራች ስርአት ከሃገራችንና ከሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ትከሻ ላይ ለማውረድ ንቅናቄው መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በሙሉ በስራ ላይ እንደሚያውለው ቃል በመግባት ስብሰባውን አጠናቋል፡፡

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ**